# የሰሜኗ ኮከብ በለዉጥ ምዕራፍ ላይ

**ደሳለዉ ጥላሁን**
(dessalew_t@yahoo.com)

አስር አለቃ አበራ ወልዱ ከ83 ዓመታት በላይ በሰሜኗ ኮብ መቀሌ ከተማ ኖረዋል።አፈር ፈጭተዉ፣ጭካ አቡክተዉ፣ ዉሃ ተራጭተዉ ባደጉባት በዚህችዉ ከተማ ዛሬ 'ማን ያርዳ የቀበረ ማን ይናገር የነበረ' እንዲሉ የትናንቷ መቀሌና የዛሬዋ መቀሌ ምንና ምን በሚል መንፈስ ሁለንተናዊ ለዉጡን ይመሰክራሉ።

የደስታ ስሜት በተላበሰ ማንነታቸዉ የዛሬዋን መቀሌ ከድሮዋ መቀሌ በምንም መልኩ ማወዳደር አይቻልም የሚሉት አስር አለቃ አበራ በከተማዋ ፎቅ እንዳይሰራ የሚከለከልበት ዘመን አብቅቶ ዛሬ አዲስ የስኬት ምዕራፍ ተጀምሯል ይላሉ።

የከተማዋን ሁለንተናዊ ለዉጥ ማንም አይቶ የሚመሰክረዉ እንደሆነ የሚናገሩት አስር አለቃ አበራ በተለይ በመሰረተ ልማት ዘርፍ የተከናወኑ እና እየተከናወኑ የሚገኙ አበረታች የልማት ስራዎች ከተማዋን ወደ ላቀ ደረጃ እያሸጋገራት ነዉ።

በሌላ መልኩ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዘዳንት የሆኑት ዶክተር ክንድያ ገብረህይወት እዚያዉ ተወልደዉ እዚያዉ ተምረዉ ዛሬም እዚያዉ የከተማዋን ለዉጥ በማጣጣም ላይ የሚገኙ ናቸዉ።

በልጅነት ዘመኔ ከልጅነት ጋደኞቼ ጋር ጫካ ደርሰን መጣን የምንለዉ አካባቢ ዛሬ መሃል ከተማ ሆኗል በማለት የልጅነት ዘመናቸዉን እንዲሁም የዛሬዋንና የድሮዋን መቀሌ በምልሰት የሚያስታዉሱት ዶክተር ክንድያ ደስታ በተቀላቀለበት የሳቅ መንፈስ መቀሌ ድሮና ዘንድሮ ምንናምን ይላሉ።

እኔም በንግግራቸዉ ላይ ጣልቃ በመግባት **እንዴት ዶክተር**? የሚለዉን ጥያቄ አስከተልሁ ዶክተር ክንድያ የዛሬዋ መቀሌ ከድሮዋ መቀሌ በስፋት እንኳ በሶስት እጥፍ ጨምራለች ብል አልተሳሳትኩምይላሉ። ዶክተሩ ቀጥለዉም በተለይ በማህበራዊ ልማት ረገድ የተመዘገቡት ለዉጦች እጅግ ከመጠን በላይ አመርቂ እንደሆኑ ይናገራሉ።

በ20ዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኘዉ ወጣት ኤልያስ ገብረማሪያም በከተማዋ ነዋሪ ከመሆኑም በላይ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ዉጤታማ ከሆኑ ወጣቶች መካከል አንዱ ነዉ።

ከምንም ነገር ተነስቶ መንግስት ያመቻቸለትን ምቹ ሁኔታ ተጠቅሞ በመስራቱ የካፒታል አቅሙ ከ2 ነጥብ 5 ሚሊዬን ብር በላይ መድረሱን የሚናገረዉ ወጣት ኤልያስ የከተማዋ ሁለንተናዊ ለዉጥ ለስራዉ ዉጤታማነት ትልቅ አቅም እንደፈጠረለት ያስረዳል።

በአንድም የሁን በሌላ መንግስት የሚከተለዉ የከተሞች ልማት ስትራቴጅ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸዉ ለማትና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያረጋግጡ፣ለኑሮ አመችና በፕላን የሚመሩ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ መሆኑን ያረጋግጣል።

ይህም በመሆኑ መንግስት ከተሞች የአካባቢያቸዉ የልማት ማዕከልና የዴሞክራሲ ተምሳሌት ሆነዉ እርስ በእርስ ተሳሰረዉና  አለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸዉን በማረጋገጥ በስኬታማ የጉዞ አቅጣጫ እንዲጓዙ በማድረግ ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ እሳቤ ስንነሳ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 778 ኪ.ሜ እርቀት ላይ የመትገኘዉ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ ከተማ መቀሌ አበረታች ሊባል በሚችል የለዉጥ ምዕራፍ ላይ ትገኛለች።

ከላይ በጽሑፌ መግቢያ ላይ እንደጠቀስሁት በከተማዋ ለረጅም አመት የኖሩት አስር አለቃ አበራም ሆነ ሌሎች እድሜ ጠገብ የከተማዋ ነዋሪዎች እንዲሁም የታሪክ ድርሳናት እንደሚናገሩትና እንደ ሚያትቱት የመቀሌ ከተማ ስያሜ በአጼ ሰይፈ አርድ ዘመነ መንግስት (1344-1377) አቡነ አብዲሳ የተባሉ መነኩሴ ወደ እንዳ መድሃኔአለም ገዳም በመምጣት መፅሃፈ ቅኔና ዝማሬን ያስተምሩ ነበር።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የእነዚህ ተማሪዎች ቁጠር እየጨመረ በመምጣቱ ቀለባቸዉንና ምግባቸዉን በአካባቢዉ ከሚገኙ የስድስት መንደር ነዋሪዎች እየሰበሰቡ እንዲመገቡ በማሰብ በቡድን በቡድን እየተከፋፈሉ እንዲሰማሩ አደረጉ።ስለዚህ አብረዉ ከመኖርና ተስማምቶ ከመስራት ጋር በተገናኘ መልኩ ለተማሪዎቹ እንዳደረጉት" ከፈሏቸዉ፣ተከፋፈሉ፣መደቧቸዉ፣አሰማሯቸዉ።" ከሚል ቃል መቀሌ የሚል ስያሜ እንደመነጨ ይነገራል።

በዘመናዊ መልኩ በአፄ ዮሐንስ 4ኛ የተቆረቆረችዉ ሰሜናዊቷ ኮከብ መቀሌ ዛሬ ከሩብ ሚሊዬን ህዝብ በላይ የሚኖርባት፣ከ54 ነጥብ 7 ስኩዌር ኪ/ሜ በላይ የመሬት ስፋት ያላትና ሞቅ ደመቅ ያለች በስኬት ምዕራፍ ላይ የምትገኝ ከተማ መሆኗን በከተማዋ የሚገኙ የስራ ኃላፊዎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይመስክራሉ።

እስከ ቅርብ አመታት ድረስ መቀሌ ከተማ  ኲሓ የምትባል አንድ የዱቄት ፋብሪካ፣አንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እዚህ ግባ የማይባሉ የተወሰኑ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣አንድ ሆስፒታል፣ ያልተሟላ መሰረተ ልማት የነበራት በአጠቃላይ በብዙ ችግሮች የተተበተበች ከተማ እንደነበረች የሚያስታዉሱት የመቀሌ ከተማ ከንቲባ አቶ ንጉሴ ገብረ ዛሬ የትናንት ችግሮች በዛሬ ስኬቶች እንደተተኩ ያስረዳሉ።

ባለፉት 20 አመታት በመንግስት፣በባለሀብቶች በከተማዉ ነዋሪዎች የጋራ ጥረት በከተማዋ በተከናዎኑ አበረታች ስራዎች ከ75 በላይ ት/ቤቶች፣ አንድ ዩኒቨርስቲ፣ አስር ኮሌጆች፣ አንድ ሪፈራል ሆስፒታል፣ 6 ሆስፒታሎች፣ 13 ከፍተኛና 12 መካከለኛ ደረጃ ያላቸዉ ክሊኒኮች፣ ከ48 በላይ መድሃኒት ቤቶች፣ ደረጃዉን የጠበቀ ኤርፖርት፣ ሆቴሎች እና የዱቄት ፋብሪካዎችን ጨምሮ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የተለያዩ ፋብሪካዎች ተገንብተዉ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ይናገራሉ።

በመብራት አቅርቦት ረገድ ከተማዋ ከ47 ሺህ ኪሎዋት በላይ ኃይል የምትጠቀምበት ደረጃ ላይ መድረሷን የሚያስረዱት ከንቲባዉ ከ133 ነጥብ 6 ኪ.ሜ በላይ በሚሸፍን እርቀት 4ሺህ የሚያህል የኀዳና መስመር መብራት ለከተማዋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የከተማዋን ህዝብ ዘመናዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ተጠቃሚ ለማድረግ በተሰሩ አበረታች ስራዎች ከ18 ሺህ 800 በላይ የቀጥታ ስልክ መስመር፣ ከ1 ሺህ 500 በላይ የገመድ አልባ ፣ ከ126 ሺህ 976 በላይ የሞባይል፣ እና ከ 5 መቶ 36 በላይ የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎቶች ለነዋሪዎች ተደራሽ መሆናቸዉን አቶ ንጉሴ ይናገራሉ።

በከተማዋ የሚገኙ 23 የፋይናንስ ተቋማት በከተማዉ እድገት የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነዉ ያሉት አቶ ንጉሴ 9 ነጥብ 5 ቢሊዬን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 1ሺህ 500 የሚሆኑ ባለሀብቶች በእርሻ፣በኢንዱስትሪ፣በኮንስትራክሽን፣ በሆቴል እና ቱሪዝም፣ በሪል እስቴት እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች በሚያከናዉኗቸዉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ከ120 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የስራ እድሎች መፈጠራቸዉን ያስረዳሉ።

የመቀሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ ኪዱ ኃይለዝጊ በበኩላቸዉ በ1943 ዓ.ም የተቋቋመዉ ማዘጋጃ ቤቱ ከቅርብ አመታት ወዲህ ለከተማዋ እድገት የሚመጣጠን ማስተር ፕላን የከተማዋን ህዝብ ባሳተፈ መልኩ እንዲዘጋጅ በማድረግ ወደ ስራ በመግባቱ ከተማዋ በእድገት ጎዳና ላይ ትገኛለች ብለዋል።

የከተማዋን መሰረተ ልማት ለማሟላት በተሰሩ ስራዎች ከ55 ኪ.ሜ በላይ የአስፓልት መንገድ እና 15 ኪ.ሜ ያህል የኮብል እስቶን ድንጋይ ንጣፍ መሰራቱን የሚናገሩት ስራ አስኪያጁ በተለይ የኮብል እስቶን ድንጋይ ንጣፍ ስራዉ የከተማዋን ስራ አጥነት ችግር በመቅረፍ ረገድ እየተጫወተ የሚገኘዉ ሚና የላቀ መሆኑን ያስረዳሉ።

በማዘጋጃ ቤቱ በተከናወነዉ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ አማካኝነት ከመሬት ጋር በተያያዘ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት በመደረጉ ይህም ከተማዋ ለተያያዘችዉ የለዉጥ ምዕራፍ አጋዥ እየሆነ ነዉ ብለዋል።

የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዉ ለህብረተሰቡ በእጣ መሰጠታቸዉን የሚገልፁት ስራ አስኪያጁ በተለይ አርንጓዴ ከተማ ለመፍጠር በሚደረገዉ ጥረት በከተማዋ ማስተር ፕላን ላይ 5 ታላላቅ የህዝብ ፓርኮች ተለይተዉ እነዚህን በቋሚነት ለማልማት አበረታች ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ይናገራሉ።

የሰሜኗ ኮከብ የመቀሌ ከተማ ዛሬ ላያት ሰዉ በየቀኑ የምትቀየር ከተማ በሚመስል መልኩ በለዉጥ የጎዞ መስመር  በመገማሸር ላይ መሆኗ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

በተለይ እንግዳ ተቀባይ የሆነዉ የከተማዋ ነዋሪ ህዝብ ሁለንተናዊ መስተጋብር ሲጨምርበት ደግሞ መቀሌ በነዋሪዎቿ የጋራ ጥረት በቀጣይም ከዚህም በላይ በእድገት እንደምትመነደግ አመላካች ነዉ።

ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን በመፍጠሯ ባለሀብቶች በተለያዩ ዘርፎች በሚያከናዉኗቸዉ በርካታ ስራዎች አበረታች ዉጤቶች እየተመዘገቡ ነዉ።

ወጣት ባለሀብት ነዉ አቶ ኑረዲን አብድል ጣፎ ባለሀብቱ በተሻለ የስኬት ምዕራፍ ላይ ከሚገኙ የከተማዋ ባለሀብቶች መካከል አንዱ ነው። ባለሀብቱ እንደሚናገረዉ መንግስት ባመቻቸዉ ምቹ የኢንቨስትመንት እድል በመጠቀሙ ከራሱ አልፎ ለበርካታ ስራ አጥ ወገኖች የስራ እድል ከመፍጠሩም በላይ በከተማዋ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ይናገራል።

በአብዛኛዉ ከዉጭ የሚመጣዉን የፓስታና መኮረኒ ምርት በአገር ዉስጥ ለማመረት በፋብሪካ ተከላ ደፋ ቀና እያለ የጋኘነዉ ወጣቱ ባለሀብት መቀሌ ድሮና ዝንድሮ እንዴት ታያታለህ ለሚለዉ ጥያቄ ከተማዋ በከፍተኛ የለዉጥ ምዕራፍ ላይ እንደምትገኝ ይናገራል።

አቶ ገብረመድህን ገብረ ማሪያም በከተማዋ በወለል ንጣፍ ምርት ላይ የተሰማሩ ባለሀብት ናቸዉ። ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በመቀሌ ከተማ ኅጆ ቀልሰዉ በመኖራቸዉ ከተማዋን በደንብ እንደሚያዉቋት የሚናገሩት ባለሀብቱ ከተማዋ በሁሉም መስክ አበረታች ዉጤቶችን እያስመዘገበች ነዉ ይላሉ።

ኢንቨስትመንት መስፋፋቱ ለከተማዋ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሆነ የሚናገሩት ባለሀብቱ በተለይ የከተማዋን የስራ አጥ ችግር በመቅረፍ ረገድ እየተጫወተ የሚገኘዉ ሚና የላቀ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ሰሜናዊቷ ኮከብ መቀሌ ለአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍ አደረጃጀት ጉልህ ጠቀሜታ ካስገኘላቸዉና የከተማዉ ነዋሪዎችም እድሉን በስፋት በመጠቀም ድህነትን መዋጋት ከቻሉባቸዉ የአገሪቱ ከተሞች አንዷ ናት። ከተማዋ ዘርፉን የስራ አጥነት ችግርን ከመቅረፍም በላይ የከተማዋን እድገት ለማስቀጠል በእጅጉ እየተጠቀመችበት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ከላይ በጽሑፌ መግቢያ ላይ እንደጠቀስኩት ወጣት ኤልያስ ገብረማሪያምን ጨምሮ ሌሎች በርካታ የከተማዋ ስራ አጥ ወገኖች ከራስ ጉርስ በዘለለ በርካታ ሊባል የሚችል ጥሪት በመቋጠር ሌሎችንም መጥቀም ጀምረዋል።

በክልሉ በሚገኙ የጥቃቅንና አንስተኛ ተቋማት ከተሰማሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች 20 በመቶ የሚሆኑት በከተማዋ የሚገኙ ሲሆን ከተማዋም በከተማት ልማት ዙሪያ ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች።

ባለዉ ዉስን ካፒታልና ሰፊ ጉልበት ዘርፉ በከተማዋ ብዙ የስራ እድል የሚፈጠርበት ከመሆኑም በላይ እየተከናወነ ለሚገኘዉ የኢንዱስትሪ ልማት ጉዞ መሰረት ነዉ የሚሉት የትግራይ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ምክትል ኃላፊና የከተማዋ የጥቃቅንና አነስተኛ የስራ ሂደት ባለቤት አቶ ይማነ ወ/ገብርኤል በቀጣይም ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት መሆኑን ይናገራሉ።

በተለይም በዘርፉ እድገት ተኮር የሆኑ ጉዳዮች ተለይተዉና ትኩረት ተሰጥቷቸዉ መሰራት በመጀመራቸዉ በቀጣይ የቴክኖሎጅ ሽግግር ከማምጣት እንጻር የሚኖራቸዉ ሚና የጎላ ነዉ።

በጥቃቅንና አንስተኛ ዘርፍም ሆነ በሌሎች ዘርፎች በከተማዋ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ከማሳካት አንጻርና ኢንዱስትሪዉ የመሪነት ሚናዉን የሚጫወበትን ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ  በከተማዋ የኢንዱስትሪ ዞን ተዘጋጅቶ አበረታች ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸዉን አቶ ይማነ ይናገራሉ።

መቀሌ በአካል ተገኝቶ ለተመለከታት በአንድም ይሁን በሌላ በከፍተኛ የለዉጥ ምዕራፍ ላይ ናት ብሎ መናገር ይቻላል።ከዚህ ባለፈም የከተማዋ ነዋሪዎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የሰሜኗ ኮከብ መቀሌ በመንግስትና በእኛ በነዋሪዎቿ ያለሰለሰ ጥረት ተቀይራለች በማለት ምስክርነታቸዉን እየሰጡ ነዉ።

በክልሉም ሆነ በከተማዋ የመጀመሪያዋ  ናት በምትባለዉ የኩሓ ዱቄት ፋብሪካ ለበርካታ አመታት እየሰሩ የሚገኙት ወ/ሮ ፀጋ በርሂ  መቀሌ ከተማ ድሮ ምንም ካልነበራት የህይወት ኑረት ወጥታ ዛሬ በሁሉም ዘርፍ ለዉጦች ተመዝግበዉ ማየታቸዉን በፍፁም የራስ መተማመን መንፈስ ይመስከራሉ።

በቀጣይ ከዚህም በላይ ለዉጥ እንደምታመጣ ባለሙሉ ተስፋነኝ የሚሉት ወ/ሮ ፀጋ በተለይም ወጣቱ ትዉልድ ከእኛ ተረክቦ የበለጠ ከተማዋን የላቀ ደረጃ እንዲያሸጋግራት እናታዊ ምክራቸዉን ይለግሳሉ።

ከተሞች ባደጉ መጠን የነዋሪዎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስር በመፍጠር ለጠንካራ ህዝባዊ አንድነት መሰረት መሆናቸዉ እሙን ነዉ።

ይህ ነባራዊ ሀቅ በሰሜናዊቷ ኮከብ መቀሌ እዉን ሆኗል ሊባል በሚችል መልኩ በሁሉም ዘርፎች አበረታች ክንዋኔዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ። ታዲያ እነዚህ መልካም ጅማሮዎች ለሌሎች የአገራችን ከተሞች በምሳሌነት የሚጠቀሱ በመሆናቸዉ በብዙኃኑ የተባበረ ክንድ ከዚህም በላይ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ሰላም።

---END---